# ቤተ ክርስቲያን በገዛ ልጆችዋ ስትፈተን

## (ቁጥር ፩)

በድረ ገጻችን የምናሰራጫቸውን መርሐ ግብሮች በተመለከተ ከምዕመናን በየጊዜው ለሚቀርቡ ጥያቄ ዎች አቅም በፈቀደ ተገቢውን መልሶችን ስንሰጥ እንደቆየን ሁሉ፤ ዛሬም የምንሰጠው መልስ «በምዕ መናን ስም» ለቀረበው ጥያቄ ነው።

በቃለ ስብከታቸው ሕይወትን የሚያለመልም ትምህርት በመስጠታቸው በሀገር ውስጥም ሆነ በምድረ አሜሪካ፣ በአውሮጳ፣ በአፍሪካ እና በአውስትራሊያ አህጉራት በሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ዘንድ ተሰሚነትና ተቀባይነትን፣ ከፍ ያለ ፍቅርና አክብሮት ያገኙትን አባት አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህን፤ እንዲሁም ሌሎችን በተመለከተ «የተወገዙ ስለሆኑ ስብከታቸው በዚህ ድረ ገጽ ላይ የሚደመጠው ለምንድን ነው?» የሚል ጥያቄ ተደጋግሞ ተነስቶአል ። ብቻ ጥያቄውን ማንም ያንሳው ማን ይህን አጀንዳ ሥራዬ ብሎ ይዞ አለ ዕረፍት የሚንቀሳቀሰው «ማኅበረ ቅዱሳን» የተባለው ድርጅት መሆኑ በግልጽ ይታወቃል። እስቲ የሌሎቹን መወገዝ ለጊዜው እናቆየውና፤ ሐዋርያዊው አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ በእርግጥ ተወግዘዋል? ተወግዘው ከሆነስ የተ ወገዙት በምን ምክንያት ነው?

በመሠረቱ አንድ ሰው በሃይማኖቱ ኑፋቄ ክህደት፤ በትምህርቱ ስሕተት ጉድለት ቢገኝበት፤ ይህ የተነ ገረበትን ሰው አቅርቦ ጠይቆና ነገሩን በአግባቡ መርምሮ፣ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት የሚችለው ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ እንጂ ትናንትና ተወልዶ በቤተ ክህነቱ ግቢ ጥላ ሥር በ ሁለት እግሩ መቆም አቅቶት ድክ ድክ ሲል የነበረው ይህ «ማኅበረ ቅዱሳን» አይደለም። አይ ሲኖ ዶሱ ምን አገባውና? ጉዳዩ የሚመለከተው እኔን ነው የሚል ከሆነም፤ ያለ እኔ ማን አለ! አጉል መን ጠራራት ማን አክሎኝነት ይሆናል። ከጻጻሱ ቄሱ እንዲሉ።

ሐዋርያዊው አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህን ግን በሃይማኖታቸው ኑፋቄ፣ ክህደት፣ በትምህርታቸው ስ ሕተት፣ ጉድለት ተገኝቶባቸዋል ተብሎ ለቅዱስ ሲኖዶስ ክስ ያቀረበባቸው ግለሰብ ወይም ክፍል የለ ም። ሲኖዶሱም ያስተላለፈባቸው ውግዘት ወይም ውሳኔ የለም። ለሚጠይቁንም ሰዎች ይህን ያገኙበት ን ማስረጃ እንዲያቀርቡልን ደጋግመን ጠይቀን ነበር፤ ነገር ግን ሊያቀርቡ አልቻሉም ወደፊትም ቢ ሆን ከቶ ሊያቀርቡ አይችሉም ምክንያቱም የተወገዙ ስላልሆነ።

ይህ «የማኅበረ ቅዱሳን» ድርጅት፣ የሀገር ቤቱ አልበቃ ብሎት፤ በውጭው ዓለም ያሉትን ምዕመናን ማወክ፣ ሥራዬ ብሎ ስለያዘው፤ ይህን ድርጊቱን እዚህ ላይ ለማሳወቅ ተገደናል። ስለዚህ አሁን ለ ጊዜው ማንነቱን አውቆ እንዲሰበሰብ ስንል ብቻ «ዜና ልደታ» ጋዜጣ በግንቦት 1997
እትሙ፤ «ማንን እንስማ?» በሚል ርዕስ፤ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት

1. ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ማትያስ - ከዋሺንግተን ዲሲ
2. ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ - ከአዲስ አበባ
3. ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ጢሞቴዎስ - ከአዲስ አበባ
4. ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ገብርኤልን - ከቨርጂኒያ

ጠይቆ ያገኘውን መልስ በዚህ ድረ ገጽ ላይ እነሆ አውጥተነዋልና ይመልከቱት።

ለብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳቱ ከቀረቡት ጥያቄዎችና ከተሰጡት መልሶች የምንረዳው ነገር ቢኖር እኚህ አ ባት አለመወገዛቸውን ብቻ ሳይሆን፤ እርሳቸው አልፈለጉትም እንጂ እንዲያውም ለማዕረገ ጵጵስናም ጭምር ታጭተው እንደነበር ነው። ታዲያ ቅዱስ ሲኖዶስ ካላወገዛቸው አውጋዡ ማን ሊሆን ነው? ሌላማ ማን ሊሆን ይችላል? ያለ እኔ ማን አለ ባዩ «ማኅበረ ቅዱሳን»ድርጅት እንጂ። አዎን «ተወ ግዘዋል፤ ተወግዘዋል» የሚለው ይህ መሠረተ ቢስ የስም ማጥፋት ዘመቻ፤ ቢጽ ሐሳውያን ልክ ሐዋር ያው ቅዱስ ጳውሎስ እየዞረ በሚያስተምርበት ሀገር ሁሉ፤ እግር በእግር እየተከተሉ በመሄድ «ወንጌ ል ያለ ኦሪት፤ ጥምቀት ያለ ግዝረት» አትረባም፣ አትጠቅምም፣ እያሉ የቅዱሱን ሐዋርያ ትምህርት ይቃወሙና ምዕመናን ያውኩ እንደ ነበር ሁሉ፤ ዛሬም እነዚሁ የ«ማኅበረ ቅዱሳን» ሰዎች እኚህን ሐዋርያዊ አባት በየአህጉሩ እየዞሩ በሚያስተምሩባቸው ቦታዎች ሁሉ እግር በእግር እየተከተሉ ረብሻ በማስነሳት እሳቸውን ይቃወማሉ፤ ምእመናን ትክክለኛውን ኦርቶዶክሳዊ እምነት ትምህርትና ሥርዓ ት እንዳይከተሉ ዕንቅፋት ሆነው ያውካሉ፣ ያወናብዳሉ። ኢያኔስና ኢያንበሬስ ሙሴን ይቃወሙ እን ደነበር ሁሉ፤ እነዚህም እውነትንና ጽድቅን ይቃወማሉ። ቢጽ ሐሳውያን ሐዋርያውን እንደሚቃወሙ ሁሉ፤ እነዚህም የፀረ ወንጌልን ትምህርት አቋም ይዘው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የምታስተም ረውን ትምህርት ይቃወማሉ።

«ተወግዘዋል» እያሉ በአባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ችግር የሚፈጥሩባቸውም ወይም ለመወገዛቸው ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡባቸው ውንጀላም፤ መምህሩ በተለያዩ ወቅቶች ካሰሟቸው ቃለ ስብከ ቶች፤ ከተቀረጹ ፊልሞች ላይ አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮችን ነጥለው ወይም ቀንጭበው (ቆራርጠው) ከ

ውስጡ በማውጣት በሚፈልጉት ዓይነት አገጣጥመው ባቀነባበሩት የሐሰት ቪዲዮ በምዕመናን ዘንድ እንዲጠሉ የሚያካሂዱባቸው ተራ ዘመቻ እኩይ መሆኑን ብዙዎች ተገንዝበውታል።

ለመሆኑ እነዚህ «ማኅበረ ቅዱሳን» በጥላቻ መንፈስ ተሞልተው፤ በቅናት ተወጥረው፤ በምቀኝነት ና ውዘው እስከዚህ የሚቃወሟቸው አባት ማን ናቸው? ትምህርታቸው፣ ቃለ ስብከታቸውስ ምን ይመስላል?

በአጭሩ አባ ወልደ ትንሣኤ ጣና ባሕር ደሴት ገብተው መጻሕፍተ ሐዲሳትን ተምረዋል። ቀጥለውም «ማኅበረ ቅዱሳን» የእኛ አባት ናቸው በማለት ከሚመጻደቁባቸውና ከሚኩራሩባቸው ከትልቁ አባት ከብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ዘንድ ዝዋይ የካህናት ማሰልጠኛ ገብተው ለሦስት ወር የሚሰጠውን ኮርስ በሚገባ አጠናቀዋል። ከዚያም የብጹዕነታቸው ትጋት፣ ጥረትና ብርታት ማርኳቸው ለአንድ ዓመት ያ ህል እዚያው ቆይተዋል። ቀጥለውም ወደ ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ገብተው፤ ለአንድ እውነተ ኛ ካህን የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ትምህርት በሚገባ ተከታትለው በዲፕሎማ ተመርቀዋል። የታላ ቁ ሐዋርያ የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርቱና መንፈሳዊ ሕይወቱ ማርኳቸው፤ ከሌላው አገልግሎት ይልቅ ፣ ቅድሚያ ለስብከተ ወንጌል ሰጥተው ያለምንም ደመወዝ፣ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ፤ ከአንዱ አ ህጉር ወደ ሌላው አህጉር፣ ደከመኝ፣ሰለቸኝ ሳይሉ እየተንከራተቱ፤ በመላው ዓለም እንደ እህል ዘር ለተበተኑት ኢትዮጵያውያን ወገኖች ወንጌልን ያስተምራሉ፣ ያጽናናሉ፣ ሚጠተ ተስፋ መንግሥተ ሰ ማያትን ይሰብካሉ።

ዋና ትምህርታቸውም፣ ኦሪትን፣ ነቢያትን፣ ከትምህርተ ወንጌል ጋር በሚገባ ያገናዘበ ሲሆን፤ በተጨ ማሪም፤

1. ቅዱሳት መጻሕፍትን
2. ፍትሐ ነገሥቱንና ሌሎቹን የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ አባቶች ትምህርት ለምሳሌ ያህል የቅዱስ ባ ስልዮስን፣ የቅዱስ ጎርጎርዮስን፣ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅንና የሌሎችን ሊቃውንት መጻሕፍት
3. በ16ኛው ክፍለ ዘመን በዐፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ካቶሊኮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ ዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን «ኦሪታዊ ናት» ሲሉ ስም ለማጥፋት ካካሄዱት ዘመቻ የተነሣ፤ ኦርቶዶክሳው ያን ሊቃውንቱ መልስ በመስጠት ያሳለፉትን ውሳኔ
4. ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የጻፉትን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በቅዱስ ሲኖዶሱ አስፈቅደው ለካህናት፣ ለሰባክያነ ወንጌል መማሪያ ማሰልጠኛ እንዲሆን ያዘጋጁትን ጽሑፍ ነው።

እኝህ አባት ነገረ ሃይማኖትን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ማለት ጌታ ከኦሪቱ ያስቀረልንን፣ ያሳለፈ ልንን፣ የሻረልንን፣ የተወልንን፣ ሁሉ ግልጥልጥ አድርገው በመልክ በመልኩ ያስቀምጡታል። ጥቅሱ ን ማስረጃውን ከፍ ብለን ከዘረዘርናቸው መጻሕፍት ጋር እያገናዘቡ ሲያቀርቡት ያረካል። ይህ የማይ ዋጥላቸው ግን ያለ እኛ ማንም ማስተማር የለበትም የሚል ምቀኝነት ያናወዛቸው፤ ምእመናንን አባሎ ቻቸው እያደረጉ አሥራቱን በኩራቱን ወደ ራሳቸው ግምጃ ቤት (ካዝና) ለማስገባት የሚሯሯጡት የ«ማኅበረ ቅዱሳን» ሰዎች ብቻ ናቸው። የእኝህን ሐዋርያዊ አባት ትምህርት የቱን ያህል ትክክል መሆ ኑን ለማረጋገጥ የሚሻ፣ የሚፈልግ ሰው፣ በየጊዜው በካሴት ያወጧቸውን ቃለ ስብከቶች ከዳር እስከ ዳር በሙሉ ቢሰማ፤ ማን እውነተኛ ማን ሐሰተኛ መሆኑን ሊረዳ ይችላል።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እየዞረ በሚያስተምር ወቅት በየሀገሩ የነበሩ አይሁድ፤ «ወንጌል ያለ ኦሪት፤ ጥምቀት ያለ ግዝረት» አትረባም፤ እንዲሁም የኦሪት ሕግጋትን ትምህርትህ ይቃወማል እያሉ አስቸግረውት ነበር። እርሱ ግን ራሱ አይሁዳዊ ስለነበር የኦሪትንና ነቢያትን መጻሕፍት ከታወቀው ገማልያል ቤት እየተማረ ስላደገ ለነገሩ ሁሉ ማስረጃ እየጠቀሰ ለመናገር ይመቸው ነበር። በተለይ ደ ግሞ ወደ ሮሜ ሰዎች የላከው መልእክቱ የተጻፈበት ዋና ምክንያት ይህን የአይሁድ ረብሻ በከንቱ እ ንደሆነ ለማስረዳት ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ሰው የሚጸድቀው የሙሴን ሕግ በመፈጸም ከሆነማ ክርስ ቶስ የሞተው በከንቱ ነው ማለት ነው እያለ ያስተምር ነበር (ገላ 2፣21)። ያንንም በተግባር ለማሳየት የክርስቶስን ወንጌል ከሚሰብካለቸው አሕዛብ ጋር ይመገብ ነበር። እንዲያውም በአንድ ወቅት ቅዱ ስ ጳውሎስ ቅዱስ ጴጥሮስ በሶርያ ከአሕዛብ ጋር ሲበላ ከርሞ ነገር ግን ወደ አይሁድ ሲመለስ አይ ሁድን ለማስደሰት ሲል በአይሁድ ፊት ከአሕዛብ ጋር አለመመገቡን አስመልክቶ ገስጾታል። ከዚህ የ ምንረዳው በኦሪቱ የተከለከሉትን ምግቦች አሁንም ተከልክለናል ብሎ መናገር የክርስትናን ትምህርት ያልተረዳን መሆናችንን ያሳያል።

እ.አ አቆጣጠር ጃንዋሪ 29 ቀን 2005 በዋሽንግተን ዲሲ በ«ማኅበረ ቅዱሳን» የተጠራውን ስብሰባ ለ ማዳመጥ ወደዚያ ሄድኩ። የስብሰባውን ቦታም ስላላወቅሁ ወደ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ብቅ ብዬ አቅጣጫ ስጠይቅ ባጋጣሚ በቤተ ክርስቲያናችን ከልጅነት ጊዜዋ ጀምሮ የምትዘምር እህት እኔ አሳይ ሃለሁ ብላ አብረን ጉዞ ቀጠልን። እኔም የስብሰባው ዓላማ ምን እንደሆነ ስጠይቃት፤ አንዳንድ መም ህራን እንደ እነ አባ ወልደ ትንሣኤ ያሉ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሠርገው ገብተው ኦርቶዶክሳ ዊ ያልሆነ ትምህርት ያስተምራሉ፤ ከነዚህም አንዱ የአሳማ ሥጋ እንዲሁም ሌላም መብላት ይቻላ ል ብለው አስተምረዋል ስትል አቋርጫት «የአሳማ ሥጋ መብላት ኩነኔ ነው ወይ? ክርስቶስ በመጣ

ጊዜ ያስፈርዳል ወይ? ብዬ ጠየኳት? እርሷም ኢትዮጵያውያን ክርስትናን ከመቀበላችን በፊት የኦሪት ን እምነት እንከተል ስለነበር እኛ በእሱ እንጠየቃለን በማለት ልታስረዳኝ ሞከረች። እንደ እርሷ አባ ባል ወይም እርሷን የመሰሉት የሚያምኑት፤ ክርስቶስ በፍርድ በተቀመጠ ጊዜ፤ ኢትዮጵያውያን የሚ ፈረድብን በልዩ ሕግ፤ ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ በሌላ መሆኑ ነው ማለት ነው። ይህ ዓይነት ተረ ት በየትም ያልተጻፈ ያልተሰማ ነው። በፍርድ ቀን ሁላችንም በአንድ ሕግ የምንዳኝና በሕገ ወንጌል የታዘዝነው በመፈጸም እንጂ በኦሪቱ አይደለም። <u>እኛ ኢትዮጵያን በኦሪቱ የተከለከሉትን ምግቦች የ ማንበላው ወይም አንዳንድ ሕግጋት የማንፈጽመው ከባሕል የተነሳ እንጂ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓ ት የተከለከሉ ሆነው አይደለም።</u> ይኸንንም እንድታዩት በ16ኛው ክፍለ ዘመን በዐፄ ገላውዴዎስ ዘመ ነ መንግሥት ካቶሊኮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን «ኦሪታዊ ናት» ሲሉ ስም ለ ማጥፋት ካካሄዱት ዘመቻ የተነሣ፤ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንቱ ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያናችን አቋም ገልጸው የሰጡትን መልስ እዚህ ላይ አቅርበናል። <u>በጣም የሚገርመው የዚህ ማኅበር አባላት ወይም ተከታዮቻቸው፤ በዘመን ከቀደሙት አባቶች የበለጠ እናውቃለን ባዮችና እነሱን ከመኮነን የማ ይመለሱ መሆናቸው አስገራሚ ነው።</u>

ስለዚህ ምእመናን አንዳንድ ወጣቶች በሚፈጥሩት የስም ማጥፋት እየተደናገራችሁ እናንተም መልሳች ሁ ተባባሪ በመሆን የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳይስፋፋ እንቅፋት እንዳትሆኑ፤ ከላይ እንደተጠቀ ሰውም ከእግዚአብሔር ልጅነት እንዳትለዩ ልትጠነቀቁ ይገባል። ሌላው ቢቀር መምህራኑን እድል ሰ ጥተናቸው ልንሰማቸውና፤ በእርግጥ እንደተባለው ከቤተ ክርስቲያናችን ውጭ የሆነ ትምህርት ካስተማ ሩ እዚያው ጠይቆ መረዳት እንጂ፤ በዚህ የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚነገረውን ብቻ ሰምቶ መነዳት አ እምሮ እንደሌለን ያስገምታል።

አሁንም «ማኅበረ ቅዱሳን» ሆነ ሌሎች በስም የማጥፋት ዘመቻ የተሰማራን ለእግዚአብሔር መንግሥ ት መስፋፋት እንቅፋት የሆንን ካለን፤ ከአሁን ጀምሮ ከእንደዚህ ዓይነት እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን ምግባር ልንቆጠብ ይገባል። ከስም ማጥፋት ይልቅ ለወንጌል መስፋፋት፤ በመክሊታችን ልናተርፍና ከ አምላካችን በረከትን ልንቀበል ልንጥር ይገባል። በዘመን የቀደሙንን የአባቶቻችን ፈለግ በመከተል፤ ትምህርታቸውን በመቀበል፤ ሕይወታቸውን ምሳሌ አድርገን የተውልንን መጻሕፍት በማገላበጥ መማር እንጂ፤ በራሳችን ስሜት ብቻ እየተመራን ይህ ማለት እንደዚህ ማለቱ ነው እያልን ሥርዓቶች፤ ሕግጋ ቶች እየፈጠርን መሄድ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል ነው። በተጨማሪም አንዳ

ንድ አዳዲስ ሥርዓቶችን የነበሩ በማስመሰል ምእመናንን ማደናገር አልፎም መከፋፈያ አድርጎ መጠ
ቀም አደገኛ ነው። አለበለዚያ «ሥርዓተ ሕግ ዘማኅበረ ቅዱሳን» የሚል አዲስ ጽሑፍ በግልጽ አው
ጥቶ፤ ምእመናንም የትኛው የአባቶች ሕግ፤ የትኛው ደግሞ የዘመኑ ወጣቶች የፈጠሩት ሕግ መሆኑን
ለይተው እንዲያውቁት ያስችላል። ነገር ግን የጥንታዊ የቤተ ክርስቲያናችን ሕግ ነው እያሉ ማደናገር
ተገቢ አይደለም። «ማኅበረ ቅዱሳንም» ስሙና ሥራው አብሮ ሊሄድ ይገባዋል እንጂ በእንዲህ ዓይ
ነት ከአንድ ተራ ሰው የማይጠበቅ ምግባር ወይም የስም ማጥፋት ዘመቻ ሊያካሂድ አይገባውም።

«ማኅበረ ቅዱሳን» በቤተ ክህነት በሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ ክፍል ሥር የተቋቋመ ክፍል
ነው። ማኅበሩ በቤተ ክህነቱ ሥር ይቋቋም እንጂ፤ ሥራውን የሚያካሄደው በተናጥል ነው። ግልጋሎቱ
ን ሲጀመር ጥሩ የነበረና ተስፋ የተጣለበት ነበር፤ ይሁን እንጂ እየዋለ፣ እያደር የሲኖዶስ
ሥራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እየገባ፣ ምእመናንን እንዲከፋፈሉ፤ መምህራን ከቤተ ክርስቲያን እንዲሰደ
ዱ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከተሰጣቸው ሥራ ድርሻ ውጭ አልፈው ሲኖዶስ ያላደረገውን እ
ንዳደረገ በማስመስል በቤተ ክህነቱ ሥልጣን ድርሻ እየገቡ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ዘላቂ ችግር እየጨ
መሩ ለመሆኑ ከቀን ወደ ቀን እየጐላ እየመጣ ነው። ለምሳሌ ያህል በየካቲት 1999 በናይሮቢ በ«ማኅ
በረ ቅዱሳን» የተፈጠረውን ችግር አስመልክቶ ከቅዱስ ሲኖዶስ የተጻፈውን ደብዳቤ አያይዘን እዚህ
ላይ አውጥተናል።

አሁንም በቅርቡ መስከረም 12 ቀን 2002 በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃና መምሪያና እንደ ደንቡ ከሆነ
በሥሩ በሚተዳደረው የ«ማኅበረ ቅዱሳን» መካከል የተፈጠረውን አለመግባበት ችግር መርምሮ መፍት
ሔ ለመፈለግ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ የማኅበሩ የሥራ አመራር አባላት እንዲሁም የሚመለከታቸ
ው የወያኔ መንግሥት ተወካዮች በተገኙበት ከፍተኛ ጉባኤ ተካሂዷል። በጉባኤውም ላይ ማኅበሩ በአ
ለፉት ዓመታት መተዳዳሪያ ደንቡን ወደ ጎን በመተው በራሱ አካሄድ በመሄድ ምን ያህል በቤተ ክርስ
ቲያናችን ላይ ጉዳት እንዳደረሰ ቀርቧል። ከተዘረዘሩትም መካከል ወጣቶችን በማነሳሳት ሰላም የሚነሳ
ችግር እንዲፈጠር ማድረጉን፤ በሐመርና ስምዐ ጽድቅ በተባሉ መጽሔትና ጋዜጣ ላይ አስፈላጊው ክ
ፍል ሳይመለከተው እርማት ሳይደረግለት ማሳተሙ ኅብረተሰቡን እያተራመሰ የሚገኝ ድርጅት እንደሆ
ነ ተገልጿል። በመጨረሻም ጉባኤው ማኅበሩ ከአሁን በኋላ በራሱ ማን አለብኝነት ብቻ እንደፈለገ
መመራት እንደማይችልና በደንቡ መሠረት በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃና መምሪያ ሥር እንዲሠራ 6
ነጥብ የያዘ ውሳኔ አሳልፏል። በተጨማሪም ከቤተ ክህነቱ አልፎ፤ የኢሀዴግ መንግሥት ተወካይ ማኅ
በሩ ከአሁን በኋላ መንግሥትንና ሕዝብን፣ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥትን ከሚያጋጭና ከሚለያይ ተግ

ባር ሊታረም እንዲገባው አስጠንቅቀዋል። ይህ እንግዲህ የሚያሳየው የዚህን ማኅበር አደገኛ እንቅስ ቃሴን ነው። ይህ የማን አለብኝነት ድርጊት ካሁኑ እልባት ካላገኘ ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ዘላቂ ችግ ር ውስጥ ይጥላታል። ስለዚህም «ማኅበረ ቅዱሳን» ስሙ ከግብሩ ጋር እንዲሄድ፤ ምእመናንን ከሚከ ፋፈል ነገር ተቆጥቦ፤ ወንጌል የሚስፋፋትበትን ትኩረት በመስጠት፤ መንፈሳዊ መጻሕፍት ታትመው በ ብዛት የሚዳረሱበትንና፤ ገዳማት የሚረዱበት ላይ ካተኮረ፤ በብዙኃኑ ምእመናን ታቅፎ፣ ተወዶ፣ የበለ ጠ ዓላማውን ከግቡ ማድረስ ይችላል። አለበለዚያ ግን ስንት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ የ ሚጠበቀው ድርጅት በከንቱ ሥራው ተጨናግፎ ምናልባትም ከቤተ ክርስቲያኗ ተሰዶ፤ የአንድ ቤተ ክ ርስቲያን ልጆች የበለጠ ተከፋፍለው የጎሪጥ እንዲተያዩ ሊያደርግ ይችላል፤ ብሎም ከቤተ ክርስቲያኗ እስከመገንጠል እንዳያደርስ ያሰጋል።

በሚቀጥለው ተከታታይ ጽሑፋችን ደግሞ «ማኅበረ ቅዱሳን» በሌሎች መምህራን ላይ ስለሚያደርገ ው የስም ማጥፋት ዘመቻና እንዲሁም ምዕመናን ለመከፋፈል ስለፈጸማቸው ድርጊቶች አስመልክቶ አጭር ዘገባ ይኖረናል።

እግዚአብሔር አምላክ ሀገራችን እንዲባርክልን በቸርነቱ እንዲጎበኘን፤ አስተዋይ አእምሮን እንዲሰጠ ንና ለወንጌለ መንግሥት መስፋፋት መሣሪያዎቹ እንድንሆን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን።

ኅዳር 2002

www.ethiopianorthodox.org team!